***ቅንጅት ዓለማቀፍ የፖለቲካ አመራር***
***አውሮፓ የትግል ቃል ኪዳኑን በማደስ ድርሻውን ይወጣ ዘንድ!***

## ታላቅ የስብሰባ ጥሪ ለቅንጅት የድጋፍ አመራር አካላትና የድጋፍ ድርጅቶች አባላት ያደርጋል

**የስብሰባ ቀን አርብ ከሰአት በኋላ ከ 3.00 PM September 15 እስከ September 17 የምሳ ሰአት ድረስ (12.00 PM)**

በቅንጅት አለም አቀፍ የቅንጅት አመራር ኮሚቴ እና በአውሮፓ የድጋፍ ድርጅቶች ትብብር በቤልጂም ብረስልስ ከተማ ውስጥ አንድ ከፍተኛ ጉባኤ ተዘጋጅቷል:: ይህ ጉባኤ አላማው በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመመካከር ቅንጅት ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ መስፈን በሃገር ቤት የሚያደርገውን ትግል በተሟላ ጉልበት እውቀት እና ሃብት ለመደገፍ የሚያስችል በአውሮፓ ውስጥ የጋራ አመለካከት፣ አንድ ወጥ የሆነ አደረጃጀት እና የተግባር አንድነት ይዞ ለመንቀሳቀስ እንዲቻል ለማድረግ ነው::

በእዚህ ስብሰባ ላይ ለውይይት ከሚቀርቡትና የጋራ አመለካከትና የተግባር አንድነት ሊያዝባቸው ከሚገባቸው ነጥቦች መሃል::

- አጠቃላይ የሃገር ቤቱ ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ
- የዴሞክራሲ እና የነጻነት ጎራው መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ጥንካሬ እና ድክመት
- የወያኔ/ኢሃዴግ አምባገነን መንግስት መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ጥንካሬ እና ድክመት
- ትብብር ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ አመሰራረት፣ መቼ፣ እንዴት፣ በነማን ለምን የሚሉትንና ከዚህ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ
- የቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር የአመሰራረት ሂደት፤ እንቅስቃሴ እና አሁን የሚገኝበት ይዞታ
- የድጋፍ ድርጅቶች አደረጃጀት ከቅንጅት መሰረታዊ መርሆዎች አንጻር
- የድጋፍ ድርጅቶች አደረጃጀት እና የአለም አቀፍ አመራር የአመለካከት፣ ድርጅታዊ እና ተግባራዊ ግንኙነት
- በአጭር ግዜ ውስጥ መከናወን በሚገባቸው እቅዶች ላይ ስምምነት እንዲደረስና መሪዎቻችንን ለማስፈታትና የዴሞክራሲ ትግሉን ለመደገፍ አውሮፓ አቀፍ ስራዎች በአስቸኳይ እንዲጀመሩ ማድርግ ይሆናል::

ይህ ስብሰባ የድጋፍ ድርጅቶች አመራር ብቻ ሳይሆኑ አቅሙ ያላቸው አባላትና ቅንጅት የቀመለትን ዓላማ በቅንነት በማራመድ ላይ የሚገኙትን ጭምር በስፋት ለማሳተፍ የተፈለገ በመሆኑ በእዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት የምትፈልጉ በሙሉ በቅድሚያ ለስብሰባው አዘጋጆች እንድታሰታውቁ አንገልጻለን::

በስብሰባው ላይ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ከተነሱ ድምጽ መስጠት የሚችሉት የየሀገሩን የድጋፍ ድረጅቶችን ወክለው የመጡት ብቻ ይሆናሉ::

የስብሰባ አዳራሽና የማረፊያ ቦታ ለማዘጋጀት የተሰብሳቢውን ቁጥር በቅድሚያ ማወቁ አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም ተሳታፊዎች በሚከተሉት የግንኙነት መስመሮች ማሳወቅ ይችላሉ።
e-mail kinijitsup@yahoo.com

ስልክ +32 494 14 73 45፣ + 474 150 84 53፣/ + 44 79606 91661

**የቅንጅት ዓለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር**
**ጳጉሜ 1998 ዓ.ም**